በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ውሳኔ


## መምህር፡- መጋቤ ሃይማኖት ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ነሐሴ ፩ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም.**

# ውሳኔ

1. <u>***መግቢያ***</u>

- በመጽሐፍ ቅዱስ በርካታ መንፈሳውያን ሰዎች የመሩት ሕይወት የተጻፈልን እኛ በሕይወት እንዴት መኖር እንዳለብን ምሳሌ ለመስጠት ነው።
    - ከአብርሃም፡- በእግዚአብሔር የማመን ሕይወት ምን እንደሚመስል
    - ከዮሴፍ፡- እግዚአብሔር በሕይወታችን የሚሠራልን ሥራና የሚያደርግልን ጥበቃ እንዴት እንደሆነ
    - ከኢዮብ፡- በመከራና በፈተና ውስጥ በትዕግሥትና በእምነት እንዴት መጽናት እንዳለብን እንማራለን።
- እንደዚሁ ከሎጥም ሕይወት የምንማረው ትምህርት አለ። ከእነዚህም የሚከተሉትን ሦስቱን በዛሬው ትምህርታችን ርዕስ ሥር እንማራለን።
    1. ውሳኔ ስለመወሰን
    2. ውሳኔያችንን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የተከተለ ማድረግ/አለማድረግ
    3. የምንወስነው ውሳኔ በሕይወታችን ውስጥ ስለሚፈጥረው ተጽእኖ
- የሎጥ ሕይወት በቅዱስ መጽሐፋችን <u>***በኦሪት ዘፍጥ ምዕራፍ 12፣ 13፣ እና 14***</u> <u>***እንዲሁም ቅዱስ ጴጥሮስ በጻፈው ሁለተኛ መልእክቱ 2:7-8***</u> ተጽፎልናል።

2. <u>***ሎጥ ማነው?***</u>

- የአብርሃም የወንድሙ ልጅ ሲሆን አብርሃም በእግዚአብሔር ሲጠራ አስከትሎት ወደ ከነዓን ወሰደው
- እንደ አጎቱ እንደ አብርሃም ባለጠጋ ነበረ<u>***። ዘፍጥ 13:2-5።***</u>
- አብርሃምና ሎጥ የተቀመጡበት ሥፍራ ስላልበቃቸው፣ ያፈሩትም ሀብት ስለበዛና ከብቶቻቸውም ስለበረከቱ መለያየታቸው ግድሆነ። <u>***ዘፍጥ 13:6-9።***</u>

# ውሳኔ

## 3. የሎጥ ምርጫ

- ሎጥ የወደደውን ለመምረጥ እንዲችል የተሰጠውን አጋጣሚ ተጠቅሞ ከላይ (ከውጪ) ሲያዩት ለምለም የሚመስለውን ለመኖርም የሚያስጎመዠውን ሥፍራ መረጠ፡፡ ‹‹ሎጥም ዓይኑን አነሣ፥ በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለውንም አገር ሁሉ ውኃ የሞላበት መሆኑን አየ እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን ከማጥፋቱ አስቀድሞ እስከ ዞዓር ድረስ እንደ እግዚአብሔር ገነት በግብፅ ምድር አምሳል ነበረ። ሎጥም በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለውን አገር ሁሉ መረጠ።›› ***ዘፍጥ 13፡10-11፡፡***
- ሎጥ በምርጫው ዓለማዊ አቅጣጫዎችን የተከተለ ነበር፡፡ መንፈሳዊውን ሚዛን ከመርሳቱ የተነሳ ውጪው የሚያስደስተውን አይቶ መረጠ፡፡ ‹‹ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።›› ቀዳ ዮሐ 2፡16፡፡
- ሎጥ ትሑትና አረጋዊ በሆነው አጎቱ አብርሃም ፊት ራሱን ዝቅ አድርጎ በየት መኖር እንዳለበት ምክር ጠይቆ መወሰን ሲገባው በስግብግብነትና በራስ ወዳድነት እንዲሁም ዓለማዊ በሆነው መንገድ ሄዶ በአብርሃም ላይ አልፎ ምርጫን መረጠ፡፡
- ሎጥ የመረጠው ምርጫ ከውጪ ሆኖ ሲታይ መልካም ቢመስልም ብዙ ሐዘንና መከራ ያስከተለበት ነበር፡፡
- ‹‹በሥጋ ምኞት፣ በዓይን አምሮታችን ስለገንዘብም በመመካት›› የምንወስናቸው ውሳኔዎች የተሳሳቱ ሲሆኑ ፍጹም የእግዚአብሔር ፈቃድ የሌለባቸው ናቸው፡፡ የሎጥ ችግርም ይኸው ነበር፡፡
- ሎጥ በየት መኖር እንዳለበት ሲወስን የእግዚአብሔርን ፈቃድ አልጠየቀም፤ እግዚአብሔርን መፈለግ ትቶ የራሱን ፍላጎት ብቻ ተመልክቶ ስለሄደ ውሳኔው በሕይወቱ ታላቅ ዋጋን አስከፍሎታል፡፡

# ውሳኔ

3. ***የሎጥ ምርጫ…***

- *ሎጥ በመረጠው ምርጫ የተነሳ በጦርነት **ዘፍጥ 14:11**፣ በምርኮ **ዘፍጥ 14:12**፣ በሰዶም ሰዎች በደረሰበት ጫናና ጭቆና **ካል ጴጥ 2:7-8**፣ በሀብትና ንብረት ውድመት **ዘፍጥ 19:15-25**፣ በሚስቱ ሞት **ዘፍጥ 19:17-26**፣ በአማቾቹ ሞት **ዘፍጥ 19:14**፣ በሴቶች ልጆቹ በተፈጸመበት ነውር **ዘፍጥ 19:30-38** ከፍተኛ ዋጋን ከፍሎ መከራን ተቀብሏል፡፡ እነዚህ ሁሉ የሆኑት ራሱ ሎጥ ጻድቅ ሆኖ ሳለ ነበር፡፡**ካል ጴጥ 2:7-8***
- *ሎጥ ጻድቅ ቢሆንም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ግኑኙነት ግን የሚጠበቀውን ያህል ጥብቅ ያልነበረበት ጊዜና ክፍተት ነበር፡፡ በዚህም ክፍተት ሎጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይከተል መንፈሳዊ ሕይወቱ ዝሎ ተገኘ፡፡ ‹‹የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ቀበሮች፥ ጥቃቅኑን ቀበሮች አጥምዱልን። ›› **መኃ 2:15፡፡***
- *በሕይወታችን የምንወስነው ውሳኔ በእጅጉ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ተጽእኖ ሥር የወደቀ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግኑኙነት ጥብቅ ከሆነ በምንወስነው ውሳኔ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስንከተል የምንገኝ ስንሆን ግኑኙነታችን ግን ደካማ ከሆነ የራሳችንን ፈቃድና የዓለምን አቅጣጫ ብቻ ተከትለን ስንወስን እንገኛለን፤ ይህም ውሳኔ እንደ ሎጥ በሕይወታችን አደገኛ ችግሮችንና ተጽእኖዎችን ይፈጥራል፡፡*
- *ከጌታችን ጋር ያለን ግኑኙነት ልልና ደካማ ከሆነ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ከፍ ባለ ደረጃ መደራደሪያ በማድረግ እናቀርበዋለን፤ ሎጥ ሌላውን ለማሸነፍ ሲል መንፈሳዊ ሕይወቱን መደራደሪያ በማድረግ ለበርካታ ጊዜያት ሲያቀርብ የተገኘውም በዚሁ የተነሣ ነው፡፡*
    1. *በመጀመሪያ ራሱን ለማዳንና ለደህንነቱ ሲል የቤቱን ደጆች ያንኳኩ ለነበሩት ሁለት የሰዶም ሰዎች ወንድ የማያውቁ ሁለት ሴቶች ልጆቹን አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ **ዘፍጥ 19:8፡፡***

3. <u>የሎጥ ምርጫ…</u>

# <u>ውሳኔ</u>

2. ‹‹ሎጥም በሰዶም በር ተቀምጦ ነበር፡፡ ***<u>ዘፍጥ 19፡1</u>*** እንደተባለው ከከተማዋ መሪዎች አንዱን ለመሆን ተመኝቶ መንፈሳዊ ሕይወቱን መደራደሪያ አድርጎ ሲሞዳሞድ ተገኝቷል፡፡
3. ሎጥ መንፈሳዊ ሕይወቱን መደራደሪያ አድርጎ በማቅረብ ከታየበት ድካም የተነሣ አማቾቹን ከከተማይቱ ጥፋት አስቀድሞ እንዲወጡ ሲነግራቸው ‹‹የሚያፌዝባቸው መሰላቸው፡፡›› ***<u>ዘፍጥ 19፡14፡፡</u>***
4. መላእክቱ ከሰዶም ጎትተው ሲያወጡት ከዓለምና ከከተማይቱ ጋር የተጣበቀ ከመሆኑ የተነሣ ወደ ተራራማው ከተማ ከመውጣት ይልቅ ለሰዶም ቅርብ ወደ ሆነችው ከተማ እንዲያስመልጡት መመላእክቱን ለምኗል፡፡ ***<u>ዘፍጥ 19፡17-24፡፡</u>***
5. የአካሉ ክፋይ የሆነች ሚስቱ የሚሆነውን ለማየት ፈልጋ ሳይሆን በሰዶም ከተማ ፍቅር የተነደፈች ከከተማይቱም ጋር የተጣበቀች ስለነበረች እየተናገረች ዘወር ብላ ስታይ ከዓለም ጋር የነበራት ጥብቅ ግኑኝነት ለንስሐ ሳያድላት ሕይወትዋን አስከፍሏት የጨው አምድ ሆና ቀርታለች፡፡ ***<u>ዘፍጥ 19፡26፡፡</u>***

4. <u>እኛስ ምርጫችንና ውሳኔዎቻችንን እንዴት እናስተካክል?</u>

- የሎጥ ታሪክ በሕይወታችን ትክክለኛ ምርጫ ለመምረጥ ብሎም ውሳኔን ለመወሰን፡-
  1. ከፍተኛ ተጽእኖ ያላቸው ምርጫዎችና ውሳኔዎች እንደሚገጥሙን
  2. ትክክለኛ ውሳኔን ለመወሰን የሚያስችሉን ምክሮችን ማወቅና መረዳት እንደሚያስፈልገንና
  3. የተሳሳተ ውሳኔ ስንወስን እንዴት ማረምና ማስተካከል እንዳለብን የሚያስተምረን ነው፡፡
- እንግዲህ የራሳችንን ምርጫና ውሳኔ በሎጥ ሕይወት አስተማሪነት እንዴት እንደምናስተካክል ሦስቱን አቅጣጫዎች መሠረት አድርገን እንመልከት፡፡

# ውሳኔ

1. ***ከፍተኛ ተጽእኖ ያላቸው ምርጫዎችና ውሳኔዎች እንደሚገጥሙን***

***እግዚአብሔርን (ኢየሱስ ክርስቶስን) መከተልን አስመልክቶ***

- በሕይወታችን ታላቁን ተጽእኖ ከሚፈጥሩ ምርጫዎች አንዱ እግዚአብሔርን (ኢየሱስ ክርስቶስን) አምነን ለመከተል መምረጣችን ነው፡፡
- ምርጫችንና ውሳኔያችን በፍርድ ቀን የሚሰጠንንና የምንቆምበትን ቦታ የሚወስን ሲሆን የምንመርጠውም እያንዳንዱ ምርጫ የራሱን ምልክቶች/አሻራዎች በሕይወታችን ያኖራል፡፡
- የእርሱ ተከታዮች በመሆናችን ዘወትር የሚያሳስበን የእርሱን ፈቃድ መፈጸማችን እንጂ የራሳችንን ሐሳብና ፈቃድ መከተላችን አይሆንም፡፡

***የትዳር ጓደኛ ምርጫን አስመልክቶ***

- ይህ እግዚአብሔርን ለመከተል ከመወሰን በማስከተል በሕይወታችን የምንወስነው ታላቅ ውሳኔ ነው፡፡
- ይህ ውሳኔ በትዳር አጋራችን ምርጫ በምድር ገነት ወይም በምድር ሲዖል መካከል በምድር በምናገኘው ደስታና በሚጠብቀን ሐዘን ላይ የምንወስንበት ነው፡፡
- በዚህ ወሳኝ ጉዳይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መከተላችንን አለመከተላችንን በውሳኔአችን እናረጋግጣለን፡፡
- የትዳር አጋር ምርጫችንና ውሳኔ በልጆቻችን ዘላቂ አስተዳደግና ስሜታዊ ማንነት ላይ አሻራውን ያሳርፋል፡፡
- በኦርቶደክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ፍቺ ፍጹም መፍትሔ ሆኖ አይቆጠርም፡፡
- ይልቁኑ ተጋቢዎቹ ለልጆቻቸው ማን አባት ወይም እናት እንደሚሆናቸው ስለወሰኑና ውሳኔውንም መቀየር ስለማይቻል ልጅ/ልጆች ከወለዱ በኋላ የፍቺን መፍትሔነት የበለጠ ተቀባይነት የሌለው ያደርገዋል፡፡

# ውሳኔ

## 1. ከፍተኛ ተጽእኖ ያላቸው ምርጫዎችና ውሳኔዎች እንደሚገጥሙን

***የጓደኛ /ባልንጀራ ምርጫን አስመልክቶ***

- ከእግዚአብሔር የሆነ የልብ ወዳጅና የቅርብ ጓደኛ ማግኘት ታላቅ በረከት ነው። እንዲህ ያለ ‹‹ወዳጅ በዘመኑ ሁሉ ይወድዳልና፡፡›› ***ምሳ 17፡17፡፡***
- መልካም ባልንጀሮች በሕይወታችን በጎ ተጽእኖን ፈጣሪዎች ናቸው፤ ያበረታቱናል፤ የመንፈሳዊ ሕይወታችንንም ደረጃ ከፍ ያደርጉታል።
- በሌላ በኩል ክፉ ባልንጀርነት የጽድቅ ጠንቅ ነው፤ ‹‹ጻድቅ ለባልንጀራው መንገዱን ያሳያል የኀጥኣን መንገድ ግን ታስታቸዋለች። ›› ***ምሳ 12፡16*** ፣ ‹‹ አትሳቱ፤ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል። ›› ***ቀዳ ቆሮ 15፡33፡፡***
- ሎጥ ክፉ ባልንጀሮችን በመምረጡ መንፈሳዊ ሕይወቱን መደራደሪያ አድርጎ አቅርቦት ነበር፤ በዚህም የተነሣ ብዙ መከራ ተቀበለ። የሎጥ ስብእናም ከዚሁ የመነጨ ማንነት ነበር።

***የምንኖርበትን ሥፍራ (አካባቢ/ከተማ) መምረጥ***

- ሎጥ የሠራው ታላቁ ስህተት የመነጨው የሚኖርበትን ሥፍራ በሚመርጥበት ጊዜ በወሰነው ውሳኔ ነው።
- የሥጋውን ፍላጎት፣ የዓይኑን አምሮትና ስለገንዘብም (ሀብቱም) ተመክቶ የሚኖርበትን ሥፍራ መረጠ። እኛ ከሎጥ ተምረን በዚህ መንገድ ከመምረጥና ከመወሰን መቆጠብ አለብን።
- የምንኖርበት ሥፍራ በመንፈሳዊ ሕይወታችን፣ በትዳር አጋራችን፣ በልጆቻችንና በአጠቃላይ በቤተሰቦቻችን መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ታላቅ ተጽእኖ ያሳድራል።
- መጥፎ ተጽእኖ በሚያሳድርብን አካባቢ እግዚአብሔርን አለመከተልን መርጠን እየኖርን በምርጫችንና በውሳኔያችን ስኬታማ መሆን ከባድ ነውና በዚህም እንጠንቀቅ።

# ውሳኔ

2. **<u>ትክክለኛ ውሳኔን ለመወሰን የሚያስችሉን ምክሮች</u>**

- የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ እናውቅና እግዚአብሔርም ነገሮችን ለይተን የምናውቅበት ጥበብ ይሰጠን ዘንድ ሳናቋርጥ በትጋት እንጸልይ፡፡
- ከእግዚአብሔር የሆኑ ክርስቲያናዊ ምክሮችን እናገኝ ዘንድ ከንስሐ አባታችን፣ ከሽማግሌዎች፣ ከወላጆቻችን፣ መንፈሳዊ ምክርን ከሚሰጡ፣ ከቤ/ክ አገልጋዮች፣ ብስለት ካላቸው ባልንጀሮቻችን ምክርን እንጠይቅ፡፡
- ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቁንም ከመጽሐፈ ምሳሌና ከመጽሐፈ ሲራክ የሚገኙ ምክሮችን እንጠቀምባቸው፡፡
- የምናደርገውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ብለን እናድርገው፡፡ ‹‹መንገድህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ፥ በእርሱም ታመን፥ እርሱም ያደርግልሃል። ጽድቅህን እንደ ብርሃን፦ ፍርድህንም እንደ ቀትር ያመጣል።›› ***<u>መዝ 36(37)፡5-6</u>***፣ ‹‹የሰው አካሄድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይጸናል፥ መንገዱንም ይወድዳል። ቢወድቅም ለድንጋፄ አይጣልም፥ እግዚአብሔር እጁን ይዞ ይደግፈዋልና። ጐለመስሁ አረጀሁም ጻድቅ ሲጣል፥ ዘሩም እህል ሲለምን አላየሁም። ሁልጊዜ ይራራል ያበድርማል፥ ዘሩም በበረከት ይኖራል።›› ***<u>መዝ 36(37)፡23-26</u>***፣ ‹‹በዚህ ፈንታ። ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል።›› ***<u>ያዕ 4፡15፡፡</u>***

3. **<u>ምርጫችን የተሳሳተ መሆኑን ስናውቅ ያልተስተካከለም ውሳኔ ስንወስን ምን እናድርግ?</u>**

- ሎጥ ከሰዶምና ከገሞራ አምልጦ ሲወጣ እንዳደረገው የእግዚአብሔር የሆነውን (ቃሉን፣ ፈቃዱን…) እንፈልግ፡፡
- ያለ መቆጠብና ያለ ማንገራገር ትክክል የሆነውን ብቻ እናድርግ፡፡ የሎጥ ሚስት ሰዶምና ገሞራን ትቶ ለመውጣት ቁጥብነትን እንዳሳየችና ይህም ሕይወትዋን እንዳስከፈላት ትዝ ይበለን!!!

# ውሳኔ

3. <u>ምርጫችን የተሳሳተ መሆኑን ስናውቅ ያልተስተካከለም ውሳኔ ስንወስን ምን እናድርግ?</u>

- ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችንን ከካደው በኂላ ያደረገውን እናስተውል፡፡
  - በመረጥነው ምርጫ የሠራነው ኃጢአት ካለ ንስሐ ገብተን ኃጢአታችንን እንናዘዝ፡፡
  - በውሳኔያችን የሠራነውን ስህተት እግዚአብሔርን ማገልገል በሚያስችለን መንገድ እንፍታው፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ካሳደደ በኂላ ያደረገውን እናድርግ
  - ጌታችን ያደረገለትን ይቅርታ (ምሕረት) ለመቀበል እንደበቃ ከስህተታችን ታርመን ለመቀበል እንብቃ፡፡
  - በቀረው ዘመናችን በተቻለን ሁሉ ለጌታችን ለእግዚአብሔር እንኑርለት፡፡
- እንግዲህ ከሁሉም የሚልቀው ስህተት በትምክህትና በተመሳሳይ ምክንያት በመረጥነው የተሳሳተ ምርጫ መቀነስ እንደሆነ እናስተውል፡፡
- ማጠቃለያ
- የሎጥ ሕይወት ትክክለኛ ምርጫን የመምረጥንና ውሳኔ የመወሰንን አስፈላጊነት ከማስተማር በተጨማሪ ምርጫችንን እንደራሳችን ፈቃድ እንዳናደርግ ያስጠነቅቀናል፡፡ የምንወስነው ውሳኔ የምንመርጠው ምርጫ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን መሠረት ያደረገና እንደ ፈቃዱም መሆን ይገባዋል፤ ለሕይወታችንንና ለድኅነታችን የሚያስፈልገንን የሚያውቅልን እርሱ ነውና፡፡
- ውሳኔያችንን በራሳችን ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ተመርኩዘን እንወስን፤ ዘላለማዊ የሆነው የኛም ሆነነ የምንወዳቸው እድል የሚወሰነው በምርጫችን ላይ ተመርኩዞ እንደሆነ አውቀን ለወደፊቱ በሕይወታችን በምንወስናቸው ወሳኝ ውሳኔዎች ሁሉ ‹‹ሎጥን›› እናስበው፡፡

የእመቤታችንን ጣዕሟን ፍቅሯን በረከቷን ያሳድርብን፡፡ አሜን!!!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org